16

ጸ/ፀ/ሮ/250/67
29/1/2005

700/2013

ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ
ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- **የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣**

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ተፈጻሚ የሚሆነው የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 16/2005 ሆኖ ከመስከረም 9 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን አፈጻጸም እንድትከታተሉ የፀደቀ 1 ጥራዝ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገባችሁም መመሪያውን እንድታስፈጽሙት እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና የሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለከተማ መሬት ልማትና ማኔጀመንት ቢሮ
- ለተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽ/ቤት
- ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ሕንፃዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ
- ለመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጀንሲ
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ
- ለከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ
- ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ
- ለድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለሚኒስትሩ አማካሪ ቡድን
- ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
- ለኦዲት መምሪያ
- ለሕግ መምሪያ

ከ/ል/ኮ/ሚ
ከ1 ጥራዝ አባሪ ጋር

3

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

ቁጥር Ref.No. H1-810 ው250/34
ቀን Date. 8/7/2003

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

ለሕግ መምሪያ
ከ/ል/ኮ/ሚ

ጉዳዩ:- **የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ**

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለአነስተኛ ከተሞች የመሠረታዊ ፕላን ዝግጅት የከተማ ፕላን አማካሪ አሀዶችን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ ቁጥር700/2013የፀደቀውን ሰነድ ከጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን አባሪ በማድረግ ልከናል።

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ
ሚኒስትር

**ግልባጭ**፣

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ኮንስትራክሽን ዘርፍ/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከተማ ልማት ዘርፍ/

**ከ/ል/ኮ/ሚ**

ስልክ/ Tel.
011-553-16-88
011-553-16-72
011-553-16-73

የፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
24134/1000

ፋክስ /Fax
011-554-12-68

ድህረ ገጽ / Web Site
WWW.mudc.Gov.et
E-Mail: mwud_sm@ethionet.et

# ለአነስተኛ ከተሞች የመሠረታዊ ፕላን ዝግጅት የከተማ ፕላን አማካሪ አህዶችን ለማቋቋም የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 700/2013

ቸር 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማውጫ


አጭር መግለጫ ........ 1

መመሪያ ቁጥር 3 /2003 ........ 3

1. አጭር ርዕስ ........ 4

2. ትርጓሜ ........ 4

3. አማካሪ አህዶችን ስለማቋቋም ........ 5

4. የመቋቋሚያ መሥፈርቶች ........ 6

5. የአመዘጋገብ ሥርዓት ........ 7

6. የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ ........ 7

7. ለምዝገባ ብቁ ያለመሆን ........ 8

8. የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት ........ 8

9. የመረጣው ሥርዓት ........ 8

10. ሥልጠና ........ 9

11. የምዝገባ ምሥክር ወረቀት አሰጣጥ ........ 9

13. የሥልጠና ወጪ ........ 10

14. ፋይናንስ ........ 10

15.በአማካሪ አህዶች ስለሚሠሩ ፕሮጀክቶች ........ 10

16. በአማካሪ አህዶች ስለሚከናወኑ የወል ፕሮጀክቶችና ክትትል ........ 11

17. የሥራ ትሥሥር ስለመፍጠር ........ 12

18. የሞያ ሥነ ምግባርና ሌሎች ደንቦችን ስለማክበር ........ 12

19. የምዝገባ የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ ........ 13

20. የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማገድ ........ 13

21. አቤቱታ ስለማቅረብ ........ 14

22. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ........ 15

23. የኮሚቴው የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ ........ 15

25. ጥብቅ ክልከላ ........ 16

26. የማስፈፀም ኃላፊነት ........ 16

27. መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 16

28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 16

# በአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ዝግጅት አማካሪዎችን በማሰልጠን ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሥርዓት ለማመቻቸት የተዘጋጀው መመሪያ

## አጭር መግለጫ

በኢትዮጵያ ከሚገኙት ከተሞች መካከል ከ85% በላይ የሚሆኑት በአነስተኛ ከተማነት ማለትም የህዝብ ቁጥራቸው ከ20,000 በታች የሆነ ነዋሪ የሚገኙባቸው ከተሞች ናቸው። በአገራችን ከ80% በላይ የሚሆነው ህዝብ የሚኖረው በገጠር አካባቢ ሲሆን የገጠር አካባቢ ነዋሪውም በአብዛኛው አገልግሎቶችን የሚጋራው ከነዚሁ ከተሞች ነው። የገጠሩን ሕዝብ ኑሮ ለማሻሻልና ልማትን ለማፋጠን እንደዚሁም የገጠርና የከተማን ትስስር ለማጠናከር የእነዚሁ አነስተኛ ከተሞች ልማት ወሳኝ ነው። በነዚሁ ከተሞች ላይም አስፈላጊውን ልማት ለማምጣት መሠረታዊ ጉዳይ የሚሆነው ከተሞቹ የሚመሩበትን የከተማ ፕላን በቅድሚያ ማዘጋጀት ነው። ይህንንም መሠረት በማድረግ ባለፉት አመታት በአነስተኛ ከተሞች ዙሪያ የተወሰኑ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። በመሆኑም ቁጥራቸው ከ483 ያላነሱ ከተሞች የፕላን ተጠቃሚ ሆነዋል። ሆኖም ፕላን ተዘጋጅቶላቸው የነበሩት ከተሞችም ቢሆኑ በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ከተሞች የፕላን ክለሣ የሚፈልጉ መሆናቸው ይታመናል።

በተመሳሳይም ቁጥራቸው ከ15,000 የማያንሱ የገጠር የቀበሌ ማዕከላት መኖራቸውም ወደፊት እነዚህ ማዕከላት ጭምር ቁጥራቸው እያደገ ሲሄድ የከተማነት መስፈርትን በማሟላት ወደ ከተማ መቀየራቸው የሚጠበቅ ነው። በተመሳሳይም ከ2000 ህዝብ በላይ ያላቸው ከተሞችም የእድገት ሁኔታ ፈጣን እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል። ከዚሁ ጎን ለጎንም ብሔር ብሄረሰቦች አካባቢያቸውን እያስተዳደሩ በመሆናቸው ለአካባቢው ልማት ቀናና ምቹ ሁኔታ በመፈጠር ላይ በመሆኑ ለከተሞቻቸው ልማት የፕላን ጉዳይን እንደ ቅድመ ሁኔታ እያስቀመጡት ይገኛል። የከተማ መሠረታዊ ካርታ ከማዘጋጀት ጋር በተያያዘም የሳተላይት ምስልን በመጠቀም በአጭር ጊዜ ለበርካታ ከተሞች መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት የሚቻልበት ሁኔታ ይታያል። በመሆኑም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እነዚሁ እያደጉ የሚገኙ ከተሞችን በፕላን እንዲመሩ ከማድረግ አኳያ አገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለዚህ እስከአሁን ባለው ሁኔታ የከተማ ፕላን ዝግጅት በአብዛኛው በመንግሥታዊ ተቋማት አቅም ላይ ባተኮረ መልኩ የሚዘጋጅና የግል አማካሪዎች ተሳትፎ

ውስንነት ይታያል። በአገሪቱ የሚገኙ እምቅ አቅም ያላቸው ባለሙያዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና ስልጠና በመስጠት ወደ መስኩ እንዲገቡና የግሉ ዘርፍ የእንቅስቃሴ ሚና ከፍ እንዲል ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም በአነስተኛ ከተሞች የመሠረታዊ ፕላን ዝግጅት ዙሪያ የሚሳተፉ የአማካሪ አህዶችን በተከታታይና በስፋት ማደራጀት አስፈላጊ በመሆኑ የሚ/ር መ/ቤቱ የማብቃት ሥራዎችን በመስራት ወደ መስኩ ለማስገባት የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

በመሆኑም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 25/1/ቸ/ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

# የአነስተኛ ከተሞች ፕላን አማካሪ አህዶችን ለማቋቋም የወጣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 3 /2003

የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ዕድገት ባስከተለው ለውጥ የተነማ እያበበ የመጡትን አነስተኛ ከተሞች የከተማ ፕላን መምራትና መቆጣጠር ምቹ የመኖሪያ አካባቢና የገጠር ከተማና የከተማ ከተማ ትስስሩን የሚያጠናክሩ ማዕከላት እንዲሆኑ ትክክለኛ ራዕይ ባለው የከተማ ፕላን መምራትና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

እነዚህን አነስተኛ ከተሞች በፕላን እንዲመሩ ማድረግ የከተሞቹን የልማትና የዕድገት፣ የመልካም አስተዳደር ማዕከላት በማድረግ ነዋሪዎቹንና በዙሪያቸው ባሉ ገጠሮች የሚኖሩትን የሀገሪቱን ህዝቦች የልማት ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ ስለታመነበት፤

በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አነስተኛ ከተሞች ፕላን የማዘጋጀት ሥራ የህዝቦችን የተመጣጠነ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የማግኘት ህገ መንግሥታዊ መብት አንደኛው ማረጋገጫ መሆኑ ስለታመነበት፤

በሀገሪቱ የተመዘገበው ፈጣን እድገት ባለቤት የሆኑት ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየአካባቢያቸውን አነስተኛ ከተሞች በፕላን መመራት ጠቀሜታ በመረዳት በየጊዜው የሚያቀርቡትን የከተማ ፕላን ዝግጅት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ከመስጠት አኳያና የከተሞች ካርታ በማተላይት ምስል በመታገዝ በአጭር ጊዜ ሊዘጋጅ የሚችልበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ላይ መደረሱ ለአነስተኛ ከተሞች ፕላን ዝግጅት መልካም አጋጣሚ ሆኖ በመገኘቱ፤

መሠረታዊ የከተማ ፕላን የሚዘጋጅላቸው አነስተኛ ከተሞች ቁጥር በርካታ ከመሆናቸው አንፃር በሀገሪቱ ያለውን የከተማ ፕላን ዝግጅት ባለሞያ እጥረት ለመቅረፍ ዕውቀቱ ያላቸውን ባለሞያዎች በመመልመል፣ በአማካሪ አህድነት በማደራጀትና አቅማቸውን በሥልጠና በመገንባት ደረጃቸውን የሚመጥን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በመስጠትና የፋይናንስ ድጋፍ አመቻችቶ በሙሉ ተነሳሽነትና በቁርጠኝነት ገብተው ውጤታማ ሥራ የሚያከናውኑበትን ሁኔታ መፍጠር ወቅቱ የሚጠይቀው ተግባር ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚህም መሠረት ባለሞያዎች የሚመረጡበትን፣ የሚደራጁበትንና የአቅም ግንባታ ሥልጠና ወስደው ብቃታቸው ተረጋግጦ ወደ ሥራ የሚገቡበትንና ወደ ሥራ ከገቡም በኋላ ስለ ሥራ አፈጻጸማቸው ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት የሀገ ማዕቀፍ ሊበጅለት የሚገባ በመሆኑ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 25/1/ ቸ / ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአነስተኛ ከተሞች ፕላን አማካሪ አሀዶች ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 700/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "አነስተኛ ከተማ" ማለት የህዝብ ብዛቱ 20000 እና ከዚያ በታች ያለው ከተማ ነው ፤

2/ "መሠረታዊ የከተማ ፕላን" ማለት እስከ 20 ሺ.ህ ሕዝብ የሚኖርባቸው ከተሞች የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለመዘርጋትና የተለያዩ የከተማ አገልግሎቶችን ለመመደብ የሚያስችላቸው ፊዚካላዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ዝርዝር ያለ መዋቅራዊ ፕላን ሲሆን ለ 10 ዓመት ያህል እንዲያገለግል የሚዘጋጅ ፕላን ነው፤

3/ "የከተማ ፕላን አዘገጃጀት ሂደት ወይም ደረጃ" ማለት የቤዝ ማፕ ዝግጅትን፣ መረጃ መሰብሰብን እና መተንተንን፣ የትንበያን፣ የዲዛይን ዝግጅትንና የሪፖርት ዝግጅትን/ፕሮፖዛል፣ የማጠናቀቂያ ሥራን፣ እንዲሁም ማፅደቅና ርክክብን ያጠቃልላል፤

4/ "አማካሪነት" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/1/ ሥር የተመለከተውን የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ እና /3/የተመለከቱትን መሥፈርቶች የሚያሟሉ ሦስት ባለሞያዎች ተቀናጅተው ለአነስተኛ ከተሞች የሚሰጡት የመሠረታዊ ፕላን ዝግጅት የማማከር ተግባር ነው ፡፡

5/ "አማካሪ አሀድ" ወይም "አሀድ" ማለት ለአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ኘላን ዝግጅት የተለያየ ሙያ ያላቸው ሶስት ባለሙያዎችን በዚህ መመሪያ ውስጥ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት በማቀናጀት የሚደራጅና ወደ ሥራ እንዲገባ እገዛ የሚደረግለት አማካሪ ድርጅት ነው፤

6/ "የምዝገባ ምሥክር ወረቀት" ማለት ብቃታቸው ተረጋግጦ ለአማካሪ አሀዶች የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማለት ነው ፤

7/ "የፕሮጀክት አይነት" ማለት በአማካሪ አሃዶች ሊከናወን የሚችል በዋናነት በሕዝብ ቁጥር ላይ በመመስረት የሚዘጋጅ የከተማ ፕላን ወይም የአካባቢ ልማት ፕላን (LDP) ፕሮጀክት ነው፤

8/ "መመሪያ" ማለት ለአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ዝግጅት የተለያየ ሙያ ያላቸውን ባለሙያዎች በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት አቀናጅቶ በአሀድነት በማደራጀት ወደ ሥራ ለማስገባት በሚኒስቴሩ የወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 ነው፣

9/ "አጠቃላይ መመሪያ" ማለት ከባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ ውጪ ለሚስተናገዱ በሥራ ላይ ያለው የምዝገባ መመሪያ ማለት ነው፤

10/ "መዝጋቢ አካል" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በአሀድነት የሚመዘገቡ አመልካቾችን ማመልከቻዎች በመቀበልና በመመርመር ለአሀዱ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው፣ ወይም እንዳይሰጠው፣ እንዲሁም የዲሲፕሊን ጉድለት ሲከሰት የምሥክር ወረቀቱ እንዲሠረዝ የሚወስን የሚኒስቴሩ የከተማ ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ነው፤

11/ "የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው" ማለት መዝጋቢው አካል የምዝገባ የምሥክር ወረቀት በመስጠት ሂደት ወይም በዲሲፕሊንና በሌሎች ምክንያቶች መዝጋቢው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ አካል ነው፤

12/ "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1/ የተመለከቱት ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሲሆን አዲስ አበባ እና ድሬዳዋን ይጨምራል።

13/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትሩ ነው።

## ክፍል ሁለት

## አማካሪ አሀዶችን ስለማቋቋምና የምሥክር ወረቀት ስለመስጠት

3. አማካሪ አሀዶችን ስለማቋቋም

1/ አንድ አማካሪ አሀድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት በአማካሪ አሀድነት ተደራጅተው የአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ዝግጅት ሥራዎችን ለመስራት ፈቃደኛ በሆኑ ባለሙያዎች ይቋቋማል።

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4/1/ የተመለከተው የሙያ ስብጥር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ አማካሪ አሀድ የባለሞያ ብዛት ሦስት ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ የተመለከተው ቢኖርም አንድ ባለሞያ ከአንድ አህድ ውጭ በአባልነት ሊመዘገብ አይችልም ::

4. የመቋቋሚያ መሥፈርቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠውን የአማካሪ አሃድ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት ከባለሙያዎች የሚጠበቅ የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድን፣ የሙያ ስብጥርን፣ የቢሮ እና ሌሎች መገልገያ መሣሪያዎችን፣ እንዲሁም የሥልጠና ቅድመ ሁኔታዎችን መሟላት ይኖርባቸዋል ::

1/ የአማካሪ አሀድ ባለሞያዎች የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድ እና የሙያ ስብጥር አንድ አማካሪ አሀድ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ የተመለከተው የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድና የሙያ ስብጥር ይዞ መገኘት ይኖርበታል ።

ሠንጠረዥ 1፤ ሙያ፣ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ

| ሙያ | ዝቅተኛው ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት | በከተማ ፕላን ዝግጅት ወይም አፈጻጸም ያለው ዝቅተኛ የሥራ ልምድ (በዓመት) |
|---|---|---|
| የስፓሽያል ፕላኒንግ ባለሙያ፤ ታውንፕላነር፤ አርክቴክት ታውንፕላነር፤ ኧርባን/ሙኒሲፓል ኢንጅነሪንግ፤ኧርባን ዲዛይን፣ ተመሣሣይ ሙያ ያለው | በተዘረዘሩት የሙያ መስኮች የባችለር ዲግሪ | 2 |
| የሶሺዮ-ኢኮኖሚ ጥናት ባለሙያ (ምጣኔ ሀብት ባለሙያ / ሶሾሎጅስት / ስታስቲሽያን/የታሪክ ባለሙያ / አንትሮፖሎጅስት / እና ተመሳሳይ ሙያ) | በተዘረዘሩት የሙያ መስኮች የባችለር ዲግሪ | 2 |
| የፊዚካልና አካባቢ ጥናት (ጅኦግራፊ/ጅኦሎጂ /ኢንቫይሮሜንት ወይም ተመሳሳይ ሙያ ያለው) | በተዘረዘሩት የሙያ መስኮች የባችለር ዲግሪ | 2 |

2/ የቢሮ እና የቢሮ መገልገያ እቃዎች ይዞታ

2.1/ ማንኛውም አማካሪ አሀድ ተመዝግቦ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሥራ መሣሪያዎች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ) 12 ካሬ ሜትር ቢሮ፣

ለ) ቢያንስ 2 ጊጋ ባይት አቅም ያላቸው ሁለት ኮምፒዩተሮች ከአስፈላጊ ሶፍት ዌሮች ጋር፣

ሐ) አንድ ኤ4 መጠን ያለው ማተሚያ፣

ረ) በተለያዩ ምክንያቶች በአንድ መምሪያ የሚሰሩ ፈጻሚዎች ቁጥር ከሦስት የሚያንስ ከሆነ የቢሮ ኃላፊው እንደስራው ቅርበት በማየት በቢሮው ውስጥ ካሉ ሌሎች የልማት እና የለውጥ ቡድኖች ጋር እንዲደራጁ ያደርጋል፤

ሰ) የለውጥና የልማት ቡድን አስተባባሪ በተከታታይ በተደረጉ ግምገማዎች እና ምዘናዎች ከፈጻሚዎች መካከል በአመለካከቱ፣ በክህሎቱና በአፈጻጸሙ የተሻለ እና በአርአያነቱ እንዲሁም በማስተባበርና በመምራት ብቃት ያለው ግንባር ቀደም ፈጻሚ መሆን ይገባዋል፤

8. የለውጥና የልማት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

1) ከአንድ በላይ የለውጥና የልማት ቡድን ባለበት መምሪያ በየግማሽ ዓመቱ የቡድን አስተባባሪ በመምረጥ ለመምሪያው ማቅረብ፤

2) የቡድኑን ዕቅድ በግማሽ ዓመት፤ በሩብ ዓመት ፣ በወር እና በሳምንት ማዘጋጀት፤

3) የቡድኑ አባላት እራስን የማብቃት ዕቅድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ ለቡድኑ አባላት እራስን የማብቃት ዕቅድ ስኬት ከቡድኑ የሚፈለገውን ድጋፍ ማድረግ፤

4) በተራ ቁጥር 2 መሰረት የተዘጋጀውን የቡድኑን ዕቅድ በየሳምንቱ በመከፋፈል አፈፃፀሙን መከታተልና መገምገም፤

5) በአባላት መካከል ስላለው በቡድን የመሥራት እንቅስቃሴ እየተወያዩ ግብረ-መልስ መለዋወጥ፤

6) ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት እና አተገባበራቸው ላይ በመወያየት መማማር፤

7) አሰራራቸውንና አፈፃፀማቸውን ሊያሻሽሉና ሊያሳድጉ የሚችሉ የፈጠራ ሃሳቦች እንዲመነጩ በማድረግ ተግባራዊነቱን መፈተሽ፣

8) የአመለካከት፣ ክህሎት እና የግብዓት ማነቆዎችን በመለየት የጋራ መፍትሔ መስጠት ፤

9) የቡድኑን አባላት ጠንካራ ጎን፣ሥነ ምግባር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣የሥራ ጥራትና የሥራ ዲሲኘሊንን በመገምገም መረጃ መያዝ፣

መ) ሦስት ወንበሮች፣

ሠ) ሦስት ጠረጴዛዎች፣

ረ) አንድ የሰነድ መደርደሪያ ።

2.2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፁትን የቢሮ መገልገያዎች በየአህዱ ማሟላት በማይቻልበት ጊዜ ወይም ወጪን ለመቀነስ ሲባል ከአንድ በላይ የሆኑ አህዶች እንደአስፈላጊነቱ ከክልል ወይም ከከተሞች አስተዳደር መ/ቤቶች በሚያገኙት ወይም ከሌሎች አህዶች ጋር በጋራ በሚገለገሉበት ጽህፈት ቤት የሚጠቀሙበት አግባብ ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይችላል።

2.3/ ሥልጠና

ማንኛውም አማካሪ አህድ በዚህ መመሪያ መሠረት ለከተማ ፕላን አማካሪ አህድ የአማካሪነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መሥፈርቶች በተጨማሪ ሁሉም አባላቱ በአንቀጽ 10/1/ የተመለከተውን ሥልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል።

## 5. የአመዘጋገብ ሥርዓት

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት መስፈርቱን የሚያሟሉና በአማካሪ አህድነት ተደራጅተው ለመመዝገብ በተናጠል ወይም በቡድን ለሚቀርቡ ባለሙያዎች የሚከናወነው ምዝገባ መዝጋቢው አካል በሚያደርገው ጥሪ መሠረት ይሆናል ።

2/ በአማካሪ አህዱ መሥራች አባላት መካከል የሚኖረው የሙያ ሥራ ክፍፍልና ተዛማጅ ጉዳዮች አህዱ በሚቋቋምበት ሕጋዊ ማህበር መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ የተመለከተው ቢኖርም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የአህዱ ተጠሪና የሥራ መሪው የአስጋሽያል ፕላኒንግ ባለሞያው ነው።

## 6. የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት ተመልምለው ለሚመረጡ ሥራ ተቋራጮች ከዚህ በታች ተዘርዝረው የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የማስታወቂያ ጥሪ ይተላለፋል።

2/ የማስታወቂያ ጥሪው በተቻለ መጠን ለሁሉም ተደራሽ ይሆን ዘንድ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው መንግስታዊ የዜና ማሰራጫዎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ መተላለፍ ይኖርበታል ።

3/ በጥሪው መሠረት ለሚቀርቡ ባለሞያዎች የተሻለ ዕድል ለመስጠት የምዝገባው

ጊዜ የሁሉንም የሀገሪቱን ክልል ርቀትና የትራንስፖርት ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ይገባዋል።

4/ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረገው ጥሪ፡-

ሀ) ስለጥሪው ዓላማ፣

ለ) በመመሪያው መሰረት ባለሞያዎችን ለመመዝገብ ማሟላት ያለባቸውን የሙያና የማቴሪያል ዝግጅቶችን ፣

ሐ) መሥፈርቶቹን አሟልተው ለሚመረጡ ሥራ ተቋራጮች ስለሚደረገው የግብዓትና የሥልጠና ድጋፍ ፣

መ) ምዝገባ የሚካሄድባቸውን ቦታና ጊዜ ፣

ሠ/ በአመልካቾች መቅረብ የሚገባቸውን ማስረጃዎች ዝርዝር፣

ረ/ በጥሪው መሠረት ተወዳዳሪዎች ስለሚያቀርቧቸው የሥራ ልምድ ማስረጃዎች የሚገልፅ መሆን ይኖርበታል ።

7. ለምዝገባ ብቁ ያለመሆን

ማንኛውም በከተማ ኘላን አማካሪ አሃድነት ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ፣

1/ የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

2/ በአባልነት ከቀረቡት የአህዱ አባላት መካከል ሥራውን ለመሥራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት መሆኑ፣ ወይም ይህ መመሪያ የሚጠይቀውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ የአህዱ የምዝገባ ማመልከቻ ተቀባይነት አይኖረውም ።

8. የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት

1/ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠ ማንኛውም ከመንግሥት ተቋማትም ሆነ ከግሉ ዘርፍ የሚመጡ የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል።

2/ አመልካች ባለሙያዎች የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ለአመልካቾች በተዘጋጁላቸው የምዝገባ ቅጽ ላይ በፊርማቸው የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።

9. የመረጣው ሥርዓት

1/ መዝጋቢው አካል ለመረጣ በተዘጋጀው የመምረጫ መመሪያ መሠረት የተመዘገቡ ባለሙያዎች ያቀረቧቸውን ሰነዶች የማጣራት እና መሥፈርቶቹን ያሟሉትን የመምረጥ ሥራ ያከናውናል።

2/ የመረጣው ሥራ ሲጠናቀቅ መዝጋቢው አካል በመሥሪያ ቤቱ ግቢና በምዝገባው ሂደት ተሳታፊ በነበሩ የክልል መ/ቤቶች ውስጥ በግልፅ በሚታይ ሥፍራ መለጠፍ ወይም እንዲለጠፍ ማድረግ ይኖርበታል።

3/ ከመረጣው ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያላቸው አመልካቾች ቅሬታቸውን ውጤቱ በማስታወቂያ ከተለጠፈበት ቀን ማግሥት ጀምሮ በሚቆጠሩ አሥር ቀናት ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 ሥር ለተመለከተው ኮሚቴ ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

10. ሥልጠና

1/ ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሠረት በአህድ አባልነት ለመመዝገብ ፍላጎት ላለው ባለሙያ በሚኒስቴሩ ለስድስት ቀን የሚሰጠውን ሥልጠና መውሰድ ይኖርበታል ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት የሚሰጠው ሥልጠና ይዘት በአነስተኛ ከተሞች መሠረታዊ ፕላን ዝግጅት ፘገድ የባለሞያዎችን ክህሎት በሚገነቡ ሙያዊ ጉዳዮችና ለፕላን ዝግጅቱ ጠቃሚነት ባላቸው ፖሊሲዎችና ህጎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ዝርዝሩ በማኑዋል ይገለጻል።

11. የምዝገባ ምሥክር ወረቀት አሰጣጥ

1/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር /1/ በተመለከተው መሠረት የተመረጡ አህዶች በሚኒስቴሩ የሚሰጠውን ሥልጠና መውሰዳቸው ሲረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ ሥር የተመለከተው የአማካሪ አህድነት የምሥክር ወረቀት ይሰጣቸዋል ።

2/ ለአማካሪ አህዱ የሚሰጠው ልዩ የምስክር ወረቀት *"ለመሠረታዊ የከተማ ፕላን ዝግጅት"* የሚል ሀረግ ይኖረዋል።

3/ የአማካሪነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት በውክልና ሊሰጥ አይችልም።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው የምሥክር ወረቀት የአምስት አነስተኛ ከተሞች ፕላን ያዘጋጀ መሆኑ ሲረጋገጥ የአህዱ አባላት በአጠቃላይ መመሪያው ለሌሎች አማካሪዎች የሚሰጠውን የአማካሪነት ምዝገባ ምሥክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

12. የአህዱ ህጋዊ ሰውነት

አህዱ ህጋዊ ሰውነት የሚኖረው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሲመዘገብ ነው።

## ክፍል ሶስት

### ስለልዩ ልዩ ድጋፎች

13. የሥልጠና ወጪ

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 10/1/ ሥር የሚሰጠው ሥልጠናና ተያያዥ ወጪዎች በሚኒስቴሩ ይሸፈናሉ።

14. ፋይናንስ

ለአንድ አማካሪ አሃድ

1/ ለቢሮ መገልገያ እቃዎች መግዣ እና ለመነሻ ሥራ ማስኬጃ የፕሮጀክቱን ዋጋ አሥር በመቶ /10%/ የሚሆን ገንዘብ አማካሪዎቹ በሚሠማሩባቸው ክልሎች ወይም ከተሞች ከሚገኙ የማይክሮ ፋይናንስ ወይም ሌሎች ተቋማት በብድር፤ እና

2/ አማካሪ አሃዶች ለየፕሮጀክቶች/ፕላን ዝግጅት የሚያስፈልጋቸውን ከፕሮጀክቱ ዋጋ ከሰላሳ በመቶ /30%/ ያልበለጠ ክፍያ ከአሠሪው ከተማ በቅድመ ክፍያ፤ የሚያገኙበት ሁኔታ በአሀዶቹና በክልሎች ወይም በከተሞች መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይመቻቻል ።

3/ አማካሪ አሀዶቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ እና / 2 / የወሰዱትን ብድር እና የቅድመ ክፍያ አስመልክቶ ስለሚያቀርቡት ዋስትና በብድር ስምምነቱና በቅድሚያ ክፍያው አፈጻጸም ስምምነት ላይ ይወሰናል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /3/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ለአማካሪ አሀዶች ለሚሰጠው ብድርና ቅድሚያ ክፍያ የሚቀርበውን ዋስትና በተመለከተ የአሀዶቹ የራስ ዋስትና ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበት አማራጭ በአሠሪ ክልሎችና ከተሞች መታየት ይኖርበታል ።

## ክፍል አራት

### በአማካሪ አሀዶች የሚሠሩ ፕሮጀክቶች፣አፈጻጸም፣ ክትትልና የሥራ ትሥሥር፤

15.በአማካሪ አሀዶች ስለሚሠሩ ፕሮጀክቶች

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የምሥክር ወረቀት በተሰጣቸው አማካሪ አሀዶች የሚከናወኑት የአነስተኛ ከተሞች ፕላን ዝግጅት ፕሮጀክቶች :

ሀ/ እስከ 5000 ሕዝብ ያላቸው፣

ለ/ ከ5001-12,000 ሕዝብ ያላቸውና፣

ሐ/ ከ12,001 እስከ 20,000 ሕዝብ ለሚኖርባቸው ከተሞች የሚዘጋጁ ፕሮጀክቶች ናቸው ።

2/ ሆኖም በንዑስ አንቀጽ /1 /የተመለከቱት ፕሮጀክቶች በአማካሪ አሀዶቹ ሊከናወኑ የሚችሉት የከተሞቹ የቆዳ ስፋት ከ1000 /አንድ ሺ ሄክታር/ ያልበለጠ እንደሆነ ነው ።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተመለከቱት እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪ አሀዶቹ በተናጠል ወይም በጋራ በአካባቢ ልማት ፕላን (LDP) ዝግጅቶች ፕሮጀክት ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

4/ በአነስተኛ ከተሞች ፕላን ዝግጅት ፕሮጀክቶች የሚውሉት የክፍያ ዘዴዎች በቁርጥ ዋጋ ወይም እንደአስፈላጊነቱ በድርድር ወይም በጨረታ ሊሆን ይችላል።

5/ ለሁሉም ፕሮጀክቶች ተፈላጊው የምዝገባ ምስክር ወረቀት ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ይሆናል።

## 16. በአማካሪ አሀዶች ስለሚከናወኑ የወል ፕሮጀክቶችና ክትትል

1/ ማንኛውም የአነስተኛ ከተማ የፕላን አማካሪ አሃድ በማንኛውም የፕላን ዝግጅት ወቅት :

ሀ) ነባራዊና የወደፊት የመሬት አጠቃቀም ካርታዎች፣

ለ) ነባራዊና የወደፊት የመንገድ ተዋረድ ካርታዎች፣

ሐ) የሶሺዮኢኮኖሚ፣ የፊዚካልና አካባቢያዊ እና ስፓሺያል ጉዳዮችን የያዘ ሪፖርት ያዘጋጃል፣

2/ ከየከተማው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አግባብነት ያላቸው የመሠረተ ልማት እና አካባቢያዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ ካርታዎችንና ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣

3/ አንድ አማካሪ አሀድ የያዘውን የፕሮጀክት መጠን 75 ፣ እና ከዛ በላይ በአግባቡ ያጠናቀቀ መሆኑ ማረጋገጫ ሲያቀርብ ለሌላ ተጨማሪ ፕሮጀክት ለመወዳደር ይችላል። ሆኖም ለአማካሪ አሀዱ ተጨማሪ ፕሮጀክቱ ሊፈቀድለት የሚችለው 75፣ እና ከዚያ በላይ ለተጠናቀቀው ፕሮጀክት የጥናት ደረጃው ፕሮፖዛል ላይ የደረሰ ከሆነና አቅርቦ ካስተቸ በኋላ በመጀመሪያ በተሰጠው አንድ ከተማ የነበረው የሥራ አፈጻጸም ተመዝኖ ብቃቱ ሲረጋገጥ ነው።

4/ በከተማ ፕላን አማካሪ አሃዶች የሚዘጋጁ መሠረታዊ ፕላኖች (ግራፊክ ዶክመንቶች)፣ እንዲሁም ሪፖርቶች እና የጥናት ሰነዶች ጥራት በከተማ ፕላን አዋጁ መሠረት በሚኒስቴሩ፣ በክልል ሥራና ከተማ ልማት ቢሮዎች ወይም

የከተማ ፕላን አሀዶች ወይም ፕላን በሚሰራላቸው ከተሞች እንዲሁም በሌሎች በሕግ አግባብነት ባላቸው ተቋማት ክትትል፣ ምርመራና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

17. የሥራ ትሥሥር ስለመፍጠር

1/ ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ መሠረት ሥልጠና ወስደው የምሥክር ወረቀት የተሰጣቸው አማካሪ አሀዶች ወደ ሥራ ገብተው የአነስተኛ ከተሞች ፕላን የሚያዘጋጁበትን የበጀት አቅርቦትና የሥምሪት ሁኔታ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ወይም የከተማ አካላት ጋር በመመካከር ያመቻቻል፡፡

2/ አማካሪ አሀዶች ለተለያዩ ክልሎች የሚመደቡበት ሁኔታ በበጀት ዝግጅትና በፍላጎት ጥያቄ ቅደም ተከተል ላይ የተመሠረተ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ የፐር ራታ አሠራርን የተከተለ ይሆናል ፡፡

3/ አሀዱን ከሥራ ጋር በማስተሳሰር ወቅት የከተማው የፕላን ዋና ጉዳይ (Planning Issue) ሆኖ የተለየው የጂኦሎጂ፣ የታሪክ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ወዘተ... በሚሆንበት ጊዜ ከአሀዱ ስብጥር ውስጥ በዋናነት የተጠቀሰውን የሙያ ዘርፍ ያካተተውን አሀድ መምረጥና መመደብ ይቻላል፡፡

## ክፍል አምስት
## የሥነ ምግባር ጉዳዮችና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

18. የሞያ ሥነ ምግባርና ሌሎች ደንቦችን ስለማክበር

1/ ማናቸውም አማካሪ አሀዶችና የየአሀዱ ባለሞያዎች በነጠላና በጋራ የሚሰጡት አገልግሎት የሚጠይቀውን ሥነ ምግባርና አገልግሎቱን ለመስጠት የፈፀሙትን ውል፣ እንዲሁም ሚኒስቴሩ ያወጣቸውን የከተማ ፕላንና የኮንስትራክሽን አስተዳደር መመሪያዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

2/ የከተማ ፕላን አሀዶች፣ ወይም የክልል ሥራና ከተማ ልማት ቢሮዎች፣ ወይም ተመሳሳይ ቢሮዎች፣ ፕላን የሚሠራላቸው ከተሞች አስተዳደር የአሀዶቹን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ከመደገፍ ጎን ለጎን ከመርሃ ግብር፣ ከጥራት እና ሌሎች የኮንትራት አስተዳደር ጋር የተያያዙ አካሄዶችን እየተከታተሉ ችግሮች በሚታዩባቸው አማካሪ አሃዶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ በአማካሪ አሀዶቹ የተፈፀመው የሥነ ምግባር

ጥሰት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝም ይህንኑ ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ የምሥክር ወረቀቱ እንዲሰረዝ ሊጠይቁ ይችላሉ።

19. የምዝገባ የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ

1/ ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሠረት ለአማካሪ አሀድ የተሰጠ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት፣

ሀ) ከሶስት አባላቱ አንደኛው ወይም ሁለቱም በማናቸውም ምክንያት በሥራው ላይ ለመገኘት የማያስችላቸው ምክንያት ሲያጋጥም፤

ለ) የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የአማካሪ አሀዱ አባላት ውስጥ መስራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት በመሆኑ አሀዱ የሚሠማራበትን ሥራ ውጤታማ አያደርገውም ተብሎ የሚታመን ሲሆን ወይም አሀዱ ሇይህ መመሪያ የሚጠይቀውን ሌሎች መስፈርቶችም ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ፤

መ) በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ህግ የአማካሪ አሃዱ የምሥክር ወረቀት ወይም የአባላቱ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሠረዝ ሲወሰን፣ በመዝጋቢው አካል ሊሰረዝ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፊደል (ሀ) በተገለጸው ምክንያት የምስክር ወረቀቱ የተሠረዘበት የአማካሪ አሀድ አባል እንደገና ከሌላ ባለሞያዎች ጋር አሀድ አደራጅቶ አሀዱን የማስመዝገብ መብቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም አባሉ በዚህ መሠረት ሊስተናገድ የሚችለው የአሀዱን አባላት መንደል ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ አሳውቆ የአሀዱን የምሥክር ወረቀት መልሶ እንደሆን ወይም በአሀዱ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በእጁ እንዲያቆየው ከመዝጋቢው አካል ፈቃድ የተሰጠው እንደሆን ነው።

20. የምዝገባ ምስክር ወረቀትን ስለማገድ

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው አማካሪ አሀድ የምስክር ወረቀቱን ካገኘ በኋላ ከሥራ አፈጻጸም ጋር የተገናኘ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ወይም አቤቱታ ሲቀርብ መዝጋቢው አካል አሀዱ የተከሰሰበትን ጥፋት ስለመፈፀሙ እስኪጣራ ድረስ የተሰጠውን የምሥክር ወረቀት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል ።

3/ ሆኖም በአንቀጽ 20 /2/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ ውሳኔ ያልተሰጠው ወይም ለኤጀንሲው ያልተሳከለት ወይም ዕገዳ ያልተነሳለት አመልካች በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳይገታ በማንኛውም ጊዜ ጥያቄውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

22. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

ሀ) የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ ተወካይ --- ሰብሳቢ

ለ) የከተማ ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ተወካይ ---- አባል

ሐ) የሕግ አገልግሎት መምሪያ ተወካይ አባል የሚገኙበት ይሆናል፡፡

2/ የኮሚቴው አብላጫ ድምጽ የሚሰጠው ውሳኔ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል ሲሆን በሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡

3/ የከተማ ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ለኮሚቴው በፀሀፊነት የሚያገለግል ሠራተኛ ይመድባል፡፡

23. የኮሚቴው የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ

ኮሚቴው

1/ አንድ የአማካሪ አሀድ በማናቸውም ምክንያቶች ባለመመረጡ ወይም የአመልካቹን ማስረጃዎች ባለመቀበል አመልካቹ የምሥክር ወረቀት እንዳይሰጠው መዝጋቢው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 20 /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠበት የዕገዳ ትዕዛዝ እንዲነሳ የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት፣

2/ አመልካቹ በሥራው ሂደት ወቅት በሚፈጽመው የዲሲፕሊን ጉድለት ከምዝገባ እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ሲወሰን የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ፣ እንዲፀና ወይም እንደገና እንዲታይ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

3/ ኮሚቴው የቀረበለትን ዉሳኔ መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚረዱ ማናቸውም ሰነዶችና ማስረጃዎችን በመስሪያ ቤቱ በኩል ማስቀረብና ማየት ይችላል፡፡

4/ ሚኒስትሩ የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሰረዝ በኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የሚቀበለው ሲሆን የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሠረዝ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**24. ስለማስታወቅ**

መዝጋቢው አካል በማንኛውም ጊዜ በአማካሪ አህዱ ላይ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን እየተከታተለ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የማስታወቅ ግዴታ አለበት።

**25. ጥብቅ ክልከላ**

1/ ማንኛውም በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የምሥክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የምሥክር ወረቀቱ የተሠረዘበት አማካሪ አህድ የምሥክር ወረቀቱ ታግዶ ባለበት ወይም ተሠርዞ ባለበት ጊዜ ውስጥ ከመዝጋቢው አካል በልዩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈቀዱ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም።

2/ መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ የተሠረዘበት ወይም የታገደበት አማካሪ አህድ የምሥክር ወረቀቱ ተሠርዞ ወይም ታግዶ ባለበት ወቅት በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተመርኩዞ ባወጣው የንግድ ፈቃድ ሲንቀሳቀስ በሚገኝ አማካሪ አህድ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አግባብ ላለው አካል ማስተላለፍ አለበት ።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**26. የማስፈፀም ኃላፊነት**

የሚኒስቴሩ የከተማ ፕላን ማስተባበሪያ ቢሮ ይህን መመሪያ የማስፈፀም ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

**27. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

**28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

ጥር 20 ቀን 2003 ዓ.ም

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር

21. መመሪያውን ስለ ማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ተልዕኮውን በበለጠ ለማሳካት የሚያስችሉ ጉዳዮች መኖራቸው ሲታመንበት በሚኒስትሩና ሚኒስትር ዴኤታዎቹ በሚሰጠው አቅጣጫ በማስፈፀም አቅም ግንባታና ለውጥ ስራ አመራር ቢሮ በኩል እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ የተሻሻለውም ክፍል ለሚኒ ካቢኔ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ በሚኒስትሩ እንዲፀድቅ ያደረጋል፡፡

22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከመስከረም 9 ቀን 2005 ዓ/ም ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር

መስከረም 2004

አዲስ አበባ

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

**የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት አጠቃላይ መረጃ**

የ________________________________________ቢሮ

የ________________________________________ መምሪያ

የቡድን ቁጥር____________________

| ተ.ቁ | የአባሉ ስም ከነአያት | ዕድሜ | ጾታ | በመደበኛ አደረጃጀት ያለው የሥራ ኃላፊነት | በልማትና ለውጥ ቡድን አደረጃጀት ያለው ኃላፊነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር**

**የለውጥና የልማት ቡድን አባላት የግምገማ መረጃ ማጠናቀሪያ**

የ________________________________ቢሮ

የ________________________________መምሪያ

የቡድን ቁጥር________________________________

የግምገማው ጊዜ ከ______________እስከ____________________ ዓ.ም

| ተ.ቁ | የአባሉም ስም ከአንያት | በልማትና ለውጥ ቡድን አደረጃጀት ያለው ኃላፊነት | የአፈጻጸም ደረጃ | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1ኛ ሳ | 2ኛ ሳ | 3ኛ ሳ | 4ኛ ሳ | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

የቡድን መሪው ስምና ፊርማ________________________________

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## ሳምንታዊ የለውጥና ልማት ቡድን የውይይት ሂደት መሙያ ቅፅ

የቢሮ ስም ____________________

የመምሪያ ስም ____________________

ቡድን ቁጥር ____________________

የቃለ ጉባኤ ቁጥር __________

1. ስብሰባው የተካሄደበት ጊዜ ______ሳምንት________ቀን_______ወር 200_____ዓ/ም
2. ስብሰባው የተካሄደበት ሠዓትከ__________እስከ____________
3. በስብሰባ ላይ የተገኙ የአባላት

| ተራ ቁ. | በስብሰባ ላይ የተገኙ የአባላት ዝርዝር | የልተገኙ አባላት ስም ዝርዝር | የልተገኙበት ምክንያት |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

4. የዕለቱ አጀንዳዎች፡-

3.1 ____________________

3.2 ____________________

3.3 ____________________

3.4 ____________________

4. የሳምንት ዕቅድ ክትትልና አፈፃፀም ግምገማ

4.1 የግብ ተኮር ዕቅድ

--------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------

4.2. የግብ ተኮር ዕቅድ ክንውን

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

4.3. የልተከናወኑ ስራዎች ከነምክንያቶቻቸው

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

4.4. በተጠናቀቀው ሳምንት የተለዩ የአመለካከት ክፍተቶች እና ክፍተቱን ለማረም የተከናወኑ ተግባራት

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

4.5. በተጠናቀቀው ሳምንት የተለዩ የክህሎት ክፍተቶች እና ክህሎት ለመገንባት የተከናወኑ ተግባራት

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

4.6. የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ ______________________________

4.6.1 የቡድን ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ______________________________

4.6.2 የቡድን አባላት ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ

| ተ.ቁ. | የአባሉ ስም | የአፈፃፀም ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

5. በዕቅድ አፈፃፀም የተለዩ ጠንከራና ደካማ ጎኖች

5.1. ጠንካራ ጎኖች ------------------------------------------------------------------------

5.2. ደካማ ጎኖች------------------------------------------------------------------------

6. በአፈፃፀም ሂደት የጋጠሙ ችግሮች እና የተለዩ ማናቆዎች

6.1. የአመለካከት ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሳቦች

6.2. የክህሎት ክፍታት እና የመፍትሔ ሀሰቦች

6.3. ሌሎች ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሰቦች

7. በዕለቱ የተላለፉ ውሳኔዎች/የተደረሰባቸው ድምዳሜዎች

7.1 የቡድኑ የቀጣይ ሳምንት ዕቅድ በግብና በግብ ተኮር ተግባራት ዝርዝር

## 7.2. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------

| ሪፖርቱን ያዘጋጀው | ሪፖርቱን ያፀደቀው |
| --- | --- |
| ስም ______________________ | ስም ______________________ |
| ፊርማ ______________________ | ፊርማ ______________________ |
| ቀን ______________________ | ቀን ______________________ |

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## ወርሃዊ የለውጥና ልማት ቡድን አቅድ አፈፃፀም መገምገሚያ ቅፅ ለቢሮዎች የሚቀርብ

የቢሮ ስም_______________________________________________

የመምሪያ ስም_____________________________________________

የሪፖርት ቁጥር____________________

1. ሪፖርቱ የሚሸፈነው ጊዜ ከ________እስከ________ወር 200_____ዓ/ም
2. የተካሄደ የውይይት መድረክ ብዛት

| ተራ ቁ. | የቡድን ዝርዝር | በመመሪያ መሰረት በወር ውስጥ የተካሄደ ውይይት ብዛት | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛሳ | 2ኛሳ | 3ኛሳ | 4ኛሳ | ድምር | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

4. የወሩ ዕቅድ ክትትልና አፈፃፀም ግምገማ

4.1 የግብ ተኮር ዕቅድ

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

4.2. የግብ ተኮር ዕቅድ ክንውን

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

4.3. የልተከናወነ ከነምክንያቱ

-----------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------

4.4 በተጠናቀቀው ወር የተለዩ የአመለካከት ክፍተቶች እና ክፍተቱን ለማረም የተከናወኑ ተግባራት

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

4.5. በተጠናቀቀው ወር የተለዩ የክህሎት ክፍተቶች እና ክህሎት ለመገንባት የተከናወኑ ተግባራት

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

4.6. የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ_______________

4.6.1 የመምሪያ ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ______________

4.6.2 በመምሪያ ስር ያሉ ቡድኖች ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ

| ተራ ቁ. | ቡድን | የአፈፃፀም ደረጃ | አስተያየት |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

4.6.3 የመምሪያው አባላት ወርሃዊ የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ

| ተራ ቁ. | ስም ዝርዝር | የስራ መደብ | በውጤት ተኮር | በራስን የማበቃት | በዙሪያ መለስ | ድምር | የአፈጻጸም ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

5. በዕቅድ አፈፃፀም የተለዩ ጠንከራና ደካማ ጎኖች

5.1. ጠንከራ ጎኖች

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

5.2. ደካማ ጎኖች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

6. በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተለዩ የክህሎትና የአመለካከት ክፍተት

6.1. የአመለካከት ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሰቦች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

6.2. የክህሎት ክፍተት እና የመፍትሔ ሀሰቦች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

6.3. ሌሎች ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሰቦች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

7. የተላለፉ ውሰኔዎች/የተደረሰባቸው ድምዳሜዎች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

7.1 የመምሪያወ የቀጣይ ወር ዕቅድ በግብና በግብ ተኮር ተግባራት ዝርዝር

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

7.2.ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

| ሪፖርቱን ያዘጋጀው | ሪፖርቱን ያፀደቀው |
| --- | --- |
| ስም_______________ | ስም_______________ |
| ፊርማ _______________ | ፊርማ_______________ |
| ቀን_______________ | ቀን_______________ |

ቅፅ 005

## የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## ወርሃዊ የለውጥና ልማት ቡድን ዕቅድ አፈፃፀም መገምገሚያ ቅፅ ለማስፈፀም አቅም ግንባታና ለውጥ ስራ አመራር ቢሮ የሚቀርብ

የቢሮው ስም________________________________

የሪፖርት ቁጥር________________________

1. ሪፖርቱ የሚሸፈነው ጊዜ ከ____________እስከ____________200___ዓ/ም
2. የተካሄደ የውይይት መድረክ ብዛት

| ተራ ቁ. | የመምሪያ እና የቡድን ዝርዝር | በመመሪያ መሰረት በወር ውስጥ የተካሄደ ውይይት ብዛት | | | | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛሳ | 2ኛሳ | 3ኛሳ | 4ኛሳ | ድምር | |
| 1 | መምሪያ | | | | | | |
| 1.1 | ቡድን | | | | | | |

3. የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ________________________________

3.1 የቢሮ ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ________________

3.2 በቢሮ ስር ያሉ መምሪያ እና ቡድኖች ዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ

| ተራ ቁ. | መምሪያ እና ቡድን | የአፈፃፀም ደረጃ | አስተያየት |
|---|---|---|---|
| 1 | መምሪያ | | |
| 1.1 | ቡድን | | |

3.3 የቢሮው አባላት ወርሃዊ የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ

| ተራ ቁ. | ስም ዝርዝር | የስራ መደብ | በውጤተ ተኮር | በራስን የማብቃት | በዙሪያ መለስ | ድምር | የአፈጻጸም ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምሪያ | | | | | | |
| 1.1 | የተገምጋሚው ስም | | | | | | |

4. በዕቅድ አፈፃፀም የተለዩ ጠንከራና ደካማ ጎኖች

4.1. ጠንከራ ጎኖች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

4.2. ደካማ ጎኖች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

5. በአፈፃፀም ሂደት የጋጠሙ ችግሮች እና የተለዩ የክህሎትና የአመለካከት ክፍተት

5.1. የአመለካከት ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሰቦች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

5.2. የክህሎት ክፍታት እና የመፍትሔ ሀሰቦች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

5.3. ሌሎች ችግሮች እና የመፍትሔ ሀሰቦች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

5.4. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------

| ሪፖርቱን ያዘጋጀው | ሪፖርቱን ያፀደቀው |
|---|---|
| ስም ________________ | ስም ________________ |
| ፊርማ ________________ | ፊርማ ________________ |
| ቀን ________________ | ቀን ________________ |

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

2/ መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ እንዲታገድ በተደረገ አሀድ ወይም የአሀድ አባል ላይ የቀረበውን ጥፋት አጣርቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት ::

3/ መዝጋቢው አካል በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለፈቃዱ መሠረዝ ፣ ስለ ዕገዳው መነሳት ወይም ሌላ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ይህንኑ ለባለጉዳዩ የጽሁፍ ውሳኔውን መስጠት ወይም በመሥሪያ ቤቱ በግልፅ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት ::

4/ በዕገዳው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ እንደሆነ ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ በማንኛውም የአሀዱ አባል በሚቀርብ ማመልከቻ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ዕግዱ ወዲያውኑ እንዲነሳ ይወስናል ::

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት ዕግድ የተሰጠበት አሀድ የዲሲፕሊን ጉዳይ በፌዴራል የግዥ ኤጀንሲ የሚታይ ሆኖ ሲገኝ መዝጋቢው አካል በዚሁ የዕገዳ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለኤጀንሲው መምራት አለበት ::

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት በሚሰጥ ዕገዳ ላይ አቤቱታ አይቀርብበትም::

7/ የአማካሪ አሀዱ ፈቃድ በአንቀጽ 19 ንዑስ ቁጥር /1/ለ/ መሠረት እንዲሠረዝ ሲወሰን ጥፋተኛው በሕግ እንዲጠየቅ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል መተላለፍ አለበት ::

## ክፍል ስድስት
## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

21. አቤቱታ ስለማቅረብ

1/ በአማካሪ አሀድነት ተወዳድሮ ያልተመረጠ ወይም የተሰጠው የምሥክር ወረቀት በዲሲፕሊን ወይም በሌላ ምክንያት እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል የተወሰነበት ወይም በአንቀጽ 20/2/ በተመለከተው ሁኔታ ዕገዳው እንዲነሳለት የሚጠይቅ አመልካች መዝጋቢው አካል በሠጠው ውሳኔ ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 መሠረት ለሚቋቋመው ኮሚቴ ውሳኔው ወይም ዕገዳው አግባብ ያልሆነበትን ምክንያት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

2/ አመልካቹ ለኮሚቴው ቅሬታውን ማቅረብ የሚችለው አለመመረጡ ከተገለፀበት ወይም ከመዝገብ እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ውሳኔ በተሰጠ ወይም ውሳኔው በማስታወቂያ ከተገለፀ በ10 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት ::